Tape No. B4161, NZ, 12/94

መሠረት መጣል

የእግዚአብሔር ቃል ስልጣን እና ኃይል

ዛሬ ማታ መዝሙር ምዕራፍ 19 ከቁጥር 12-14 ያለውን ብንባብ እናውጃለን፤እነርሱም የመዝሙር የመጨረሻዎቹ ሦስት ቁጥሮች ናቸው።እነዚህ ቃላት የዳዊት ጸሎቶች ናቸው፤ለብዙ አመታት እራሳችን ስንጸልይ የኖርነው ጸሎት ነው። አንዳንዱ መልሶች በጣም ያስገርሞናል ምክንያቱም የሚጀምሩት "ስሕተትን ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ።" በሚል ነውና። ይህንን ጸሎት መጸለይ ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ እግዚአብሔር ወደ ብርሃን ያመጣቸውን የተሰወሩ ኃጢያቶቼን ወደ ኋላ ተመልሼ ስመለከት በጣም እገረማለሁ። ስለዚህ አሁን እንጸልያን፤እንዲሁም የመጨረሻውን ቁጥር በመጸለይ ከእኛ ጋር እንዲቀላቀሉ እንጋብዝዎታለን።

ስሕተትን ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ።
የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ፤ የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ÷ ከታላቁም ኃጢአት እነጻለሁ።
አቤቱ÷ ረድኤቴ መድኃኒቴም÷ የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ በፊትህ ያማረ ይሁን።

እሺ። አሁን፤በመጨረሻው ቁጥር ከእኛ ጋር ይቀላቀሉ ዘንድ እንወዳለን። ደህና፤አሁን እንጸልይ። እግዚአብሔር በምትናገሩት ቃል ስለሚይዛችሁ ካልገባችሁ መጸለይ የለባችሁም። አሁን ቃላቱን ሐረግ በሐረግ እንናገራለን፤ስለዚህ እኛ ከተናገርን በኋላ እናንተ ትከተላላችሁ። እሺ?

አቤቱ÷ ረድኤቴ መድኃኒቴም÷ የአፌ ቃልና/የልቤ አሳብ/በፊትህ ያማረ ይሁን።

አሁን እንደገና በአንድነት እንናገራለን፤እሺ። ተዘጋጅተዋል?

አቤቱ÷ ረድኤቴ መድኃኒቴም÷ የአፌ ቃልና/የልቤ አሳብ/በፊትህ ያማረ ይሁን።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

እንግዲህ አሁን የዚህ ምሽት የትምህርት ርዕስ ወደሆነው "የእግዚአብሔር ቃል ስልጣንና ኃይል" ወደሚለው እንሸጋገራለን።

ከዚህ ቀደም በነበረኝ ክፍለ ጊዜዬ "የእግዚአብሔር ቃል" በሚለው ርዕስ ውስጥ የሚሰራ ሁለት የተለያዩ መንገዶች እንዳሉ ነግሬአችኋሁ። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የሚሰራ ነው፤እያንዳንዳቸው የእግዚአብሔር ቃል ተብለው ይጠራሉ። ይህም በኢየሱስ እና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል የተሟላ ማንነት እንዳለ

ያሳያል። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር በጽሑፍ የተቀመጠ ቃል ነው፤ኢየሱስ የእግዚአብሔር የግል ቃል ነው። እኛም ከኢየሱስ ጋር በትክክል ለመገናኘት ከፈለግን፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በትክክል መዛመድ አለብን። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በተሳሳተ ግንኙነት ውስጥ ሆነን በትክክል ከኢየሱስ ጋር ልንገናኝ አንችልም። ስለዚህ በዚህ ምሽት እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል ስልጣንና ኃይል የሚለውን መሪ ሃሳብ ማቅረብ እፈልጋለሁ።

ከሥልጣኑ ጉዳይ ለመጀመር፤ቆም ብላችሁ ካሰባችሁ፤ሥልጣን (authority) የሚለው ቃል ደራሲ ወይም author ከሚለው የኢንግሊዘኛ ቃል የመጣ ነው። በሌላ አባባል፤የማንኛውንም ሥራ ሥልጣን የደራሲው ሥልጣን ነው፤ እሱ ለሚያደርገው ነገር ሁሉ ሥልጣን የሚሰጠው ደራሲው ነው። ስለዚህ የቅዱሳን መጻሕፍት ደራሲ ማን እንደሆነና፤የመጽሐፍ ቅዱስ ደራሲ ማን ነው? የሚለውን ማወቅ ያስፈልገናል፤ መጽሐፍ ቅዱስ በ 2ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 ለዚህ ጥያቄ መልስ ይሰጣል።

> የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ÷ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።

ስለዚህ ፍጹም እና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጃችሁ መሆን ከፈለጋችሁ፤ምንጩ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ በእግዚአብሔር መንፈስ አነሳሽነት እንደተጻፉ ይናገራል። የግሪኩ ቃል "የእግዚአብሔር እስትንፋስ" ይለዋል።

እንግዲህ እስትንፋስ የሆነው ቃልና የመንፈሱ ቃል አንድ ናቸው። ስለዚህ፤ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የእግዚአብሔር መንፈስ እስትንፋስ ናቸው ማለት ነው። በሌላ አነጋገር፤ከሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በስተጀርባ ያለው ስልጣን የመንፈስ ቅዱስ ሥልጣን ነው። እሱ የመጨረሻው ደራሲ ነው።እሱ በርካታ ልዩ ልዩ መንገዶችን እና መሳሪያዎችን ተጠቅሟል፤ነገር ግን ከእነርሱ ጀርባ ያለው ራሱ እግዚአብሔር የሆነው የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ነው።

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን አንቀበልም ስንል የራሱን እግዚአብሔርን ሥልጣንን አንቀበልም እያልን ነው።

እንግዲህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጡ እንጂ ጥቂቶቹ ብቻ እንዳልሆኑ ይናገራል። አንዳንድ ሰዎች በትክክል ስልጣን የላቸውም ብለው በሚያስቧቸው ሰዎች የተጻፈውን ምንባብ ያስወግዱታል። ነገር ግን ይህ ከቅዱሳት መጻሕፍት መስመር ላይ የሚሄድ አይደለም፤ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ራሱ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በእግዚአብሔር የተጻፉና ቅዱሳት መጻሕፍት በሙሉ ጠቃሚ መሆናቸውን ይናገራል። በሌላ አነጋገር፤ጥቅም የላቸውም ብላችሁ የምትጥሉት ምንም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የለም። እንደ ዕዝራ እና ነህምያ ያሉ ቅዱሳን መጻህፍቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው። መጋልየ መጋልይ ዘሰሎሞን በጣም

ጠቃሚ ነው። እንዲሁም ነቢዩ ናሆም በጣም አስፈላጊ ነው። በደንብ በታወቁት ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ብቻ አታተኩሩ፤ሁሉም እንደሚያስፈልጉ አስቡ፤ምክንያቱም እንደዚያ ማሰብ ትክክል ስላልሆነ ነው።

በሚገባ የእውቀት ዝግጁነት እንዲኖራችሁ ከፈለጋችሁ፤ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ መሞላት ይኖርባችኋል። ብዙ አመታትን ይወስድብዎታል፤ይሁን እንጂ እያደገ የሚሄድ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት ስታሰላስሉ፤ስታጠኑ እና በህይወታችሁ ላይ ተግባራዊ ስታደርጉት ከጥንካሬ ወደ ጥንካሬ መሄድ ትችላላችሁ። በመሠረቱ ላይ መገንባት ማለት የእግዚአብሔርን ቃል መስማት እና ማድረግ ስለመሆኑ ኢየሱስ የተናገረውን ማስታወስ ይኖርባችኋል። መስማት ብቻ ሳይሆን መስማት እና ማድረግ ያስፈልጋል።

እንግዲህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን በተመለከተ፤አንድ ብቻ የተፈቀደ አስተርጓሚ አለ፤እርሱም ጸሐፊው ብቻ ነው። በዚያ ስፍራ ላይ ስሜ ያለባቸው በርከት ያሉ መጽሐፍት ልታገኙ ትችላላችሁ፤ እኔ ጸሃፊ ነኝ። መጽሐፍቶቹን አንብባችሁ ግልጽ ያልሆነላችሁ ነገር ካለ፤በቂ የሆነ የማማከር አገልግሎት ለማግኘት ትክክለኛው ሰው እኔ ነኝ፤ ምክንያቱም መጽሐፍቶቹ የሚሉትን በሚገባ የማውቀው እኔ ነኝና። መስራት እንደሚገባኝ ግልጽ አድርጌ አልሰራሁትም እያልኩ አይደለም፤ነገር ግን ምን ለማለት እንደፈለግሁ አውቃለሁ። እንዲሁም በተመሳሳይ የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምን እንደሚል ለማወቅ ከፈለጋችሁ፤ደራሲውን ማማከር አለባችሁ። መጽሐፍ ቅዱስን ለመተርጎም ሥልጣን ያለው እርሱ ብቻ ነውና።

ጴጥሮስ በ2ኛ ጴጥሮስ 1፤20-21 እንዲህ ይላል፤

ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለግዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፤. . .

ማንም ሰው ፤ "ይህና፤ይህ ምን እንደሚል እኔ አውቃለሁ" ሊል አይችልም። ለመተርጎም ብቸኛ ስልጣን ያለው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው። እናም እንዲህ በማለት ይቀጥላል፤

"ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና÷ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።

እንደገና ጳውሎስ የተናገረውን ጴጥሮስ ደግሞ መልሶ ይደግመዋል፤ከመጽሐፍ ቅዱስ ጀርባ ያለው ስልጣን፤እንዲጻፍ ምክንያት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነው።

አሁን እንዲህ በጣም ምክንያታዊ ሆናችሁ እንዲህ ልትሉ ትችላላችሁ፤ "ዳሩ ግን መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች በጣም ደካማ እና ሊወድቁ የሚችሉ ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱስ እንኳን የሰሩትን በርካታ ሐጢያቶቻቸውን መዝግቦታል።"

መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉ ሰዎች ሐጢያት ተጽፎ መገኘቱ ያ የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኝነት የሚያሳይ ምልክት እንደሆነ አስባለሁ። ዛሬ በርካታ ሰዎች ሐጢያታቸውን ይሸፋፍናሉ እንጂ አይገልጡትም፤እራሳቸውን የማይወድቁ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ። የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሃፊ ያንን አያደርግም። አብዛኛውን መዝሙረ ዳዊትን የጻፈው ዳዊት እንኳን ከባድ ሐጢያቶቹ ሁሉም እንዲያነበው ተመዝግበው ተቀምጠዋል።

ስለዚህ፤መጽሐፍ ቅዱስን የጻፉት ሰዎች ፍጹማን ካልነበሩ፤መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ፍጹም ሊሆን ይችላል? ለዚህ ጥያቄ የሚሆን በጣም ቆንጆ መልስ በመዝሙር 12፤6 ላይ ተሰጥቷል፤እስቲ ቀለል ብሎ የተቀመጠውን ጥቅስ እንመልከት።

በምድር ላይ እንደ ተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ ብር የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ቃላት ናቸው።

ሰዎች ብረትን ለማጥራት ይጠቀሙበት የነበረው ትንሽ ስዕል ነው። እነሱ የሸክላ ምድጃ ይሠራሉ፤በውስጡም እሳት ያቀጣጥላሉ፤ ከዚያም ብረቱን ይጸዳ ዘንድ በእሳት ውስጥ ያኖሩታል። ስለዚህ በዚያ ስዕል ውስጥ ሦስት ነገሮች ታገኛላችሁ። የሸክላ ምድጃ፤ ይህም ሰው የሆነ መሳሪያ ነው፤ ሸክላ ብቻ ነው። ብሩን የሚያነጻው ደግሞ እሳት የሆነው መንፈስ ቅዱስ ነው፤ያም መልዕክት ነው። ስለዚህ ፍጹማን ያልሆኑ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች በእግዚአብሔር የተጠነሰሰውን እና ባለስልጣን የሆነውን እግዚአብሔርን መልዕክት ለማምጣት መንገዶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይነግረናል። ያንን እንደገና ልናገር፤ ሸክላው ሰው ነው። እሳቱ መንፈስ ቅዱስ ነው። ሰባት ጊዜ በእሳት ወስጥ አልፎ የነጻው ብር ፍጹም ንጹህ የሆነው፤የእግዚአብሔር መልዕክት ነው።

ቁጥር ሰባት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከሁለት ነገሮች ጋር ያስተሳስረናል፤እነርሱም መንፈስ ቅዱስ እና ፍጹምነት ናቸው።ፍጹምነት የሚመጣው በመንፈስ ቅዱስ ነው።

ስለዚህ፤መጽሐፍ ቅዱስ፤ከሸክላ እቃ የመጣ ቢሆንም—ደካማ፤ፍጹም ያልሆኑ፤ሐጢያተኛ የሆኑ ወንዶች እና ሴቶች —ሰባት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ነጽተዋል።ይህ ሙሉ በሙሉ የሚታመን ነው።

አሁን የኢየሱስን የራሱን ሃሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ መመልከት አለብን ምክንያቱም ለእኛ ደቀመዝሙሩ ለሆንን እሱ ምሳሌ ነውና። እሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ደህና፤ በዚህ ማለዳ መጽሐፍ ቅዱስን ተመልክተናል፤ዳሩ ግን የዮሃንስ ወንጌል ምዕራፍ 10፤ቁጥር 35 እንደገና እንመለከታለን። ሌሎችን ቁጥሮችን መመልከት

አያስፈልገንም።

ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለላቸው. . . መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና—እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው÷. . .”

ዛሬ ጠዋት ተናግሬአለሁ ነገር ግን እንደገና ደግሜ ልናገረው እወዳለሁ፤በዚያ፤ኢየሱስ ለተከታዮቹ ከዚያ ጊዜ ጀመሮ ይጠቀሙበት የነበረ

ሁለት ርዕሶችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ሰጥቷል፤እነሱም የእግዚአብሔር ቃል እና ቅዱሳን መጻህፍት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ሲል የእግዚአብሔር

ቃል ማለት ነው፤ያም ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ማለት ነው። ከሰው የመጣ ሳይሆን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ ነው።

ቅዱሳን መጻህፍት ሲል በጽሁፍ ተመዝግቦ የተቀመጠ ማለት ነው። እግዚአብሔር በጽሁፍ ተመዝግቦ ያልተቀመጡ በርካታ ነገሮች አሉት፤

ዳሩ ግን ቅዱሳን መጻሐፍት ተመዝግበው የተቀመጡት ለእኛ ለልዩ ጥቅማችን እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯል። ለደህንነታችን የሚሆን

የሚያስፈልጉንን ሁሉንም ነገሮችን ይዘዋል።

ስለዚህ በዚህ ማለዳ የኢየሱስ ሃሳብ በዚያ ሃረግ ውስጥ ተጠቃሎ ተመልክተናል፤ነገር ግን መድገሙ መልካም ነው “መጽሐፍ ሊሻር አይችሉምና።” “ሊሻር አይችሉም።” ከሚለው ቀላል ሃርግ የበለጠ የመጽሐፍን ስልጣን ሊገልጽ የሚችል የለም።

በዚህ ማለዳ ያደረግነውን በዚህ ምሽት እንድንደግመው እጋብዛለሁ፤እነዚያን ቃላት ደግማችሁ ተናገሩት፤መጽሐፍት ለሻሩ አይችሉምና።

አንድ ግዜ ተናገሩት፤

መጽሐፍት ሊሻሩ አይችምና።

እንግዲህ አሁን አስታውሱ፤እግዚብሔር በተናገራችሁት ተጠያቂ አድርጎ ይይዛችኃል፤ምክንያቱም በሁሉም የህይወታችሁ ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን አንድትቀበሉ ይጠበቃል።

አሁን ኢየሱስ መጽሐፍትን እንዴት አንድተጠቀመ እንመልከት። እንግዲህ እዚህ እሱ አሁንም ምሳሌ ነው። ወደ ማቴዎስ የ4ኛው ምዕራፍ እንመለሳለን፤እንግዲህ ኢየሱስ በምድረበዳ በሰይጣን በተፈተነ ጊዜ የሆነውን እንመለከታል። ማቴዎስ ምዕራፍ 4፤ ነገር ግን ከምዕራፍ 3 መጀመር ያስፈልገናል። ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሐንስ እንዴት እንደተጠመቀ በምዕራፍ 3 ተመዝግቦ ይገኛል።

ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ ወጣ፤ እነሆም÷ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤

አስፈላጊ ስለሆነ ያንን አስተውሉ። መንፈስ ቅዱስ በእሱ ላይ መጣ። መንፈስ ቅዱስ ለበርካታ ጊዜ በአንዳንዶቻችን ላይ ወርዶ ያውቃል፤ይሁን እንጂ እሱ ሁልጊዜ በእኛ ላይ አልቆየም ይሆናል ምክንያቱም እሱ በእኛ ዘንድ መኖር አንዳይችል የሚያደርጉ ነገሮችን እንናገራለን እንዲሁም እንተገብራለን። ዳሩ ግን ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝን ወይም ትቶት አንዲሄድ የሚያደርግ ነገር አልተናገረም ወይም አላደረገም።

“እነሆም÷ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ÷ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።”

አሁን እኔም እናንተም ልናስብ እንችላለን፤ደህና፤ ከዚያም በኋላ ኢየሱስ በእውነት ቀላል የሆነ ጊዜ ይኖረዋል። እሱ የአባቱ እና የመንፈስ ቅዱስ እንዲሁም የመጥምቁ ዮሐንስ ድጋፍ አለው፤ዳሩ ግን ያ አይደለም፤ቀጣዩ የሆነው ነገር ለአርባ ቀንና ሌሊት ጾሞ በሰይጣን ሲፈተን ራሱን በምድር በዳ ማግኘቱ ነው። እናም እባካችሁ የእግዚአብሔር በረከት ሁልጊዜ ህይወትን ቀላል ያደርጋል ብላችሁ አታስቡ በእርግጥ፤በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ህይወትን ይበልጥ አስቸጋሪ ሊያረግ ይችላል። ምክንያቱም ሰይጣን እግዚአብሔር የቀባቸውን በጣም ጠንክሮ ስለሚዋጋቸው ነው።

በሉቃስ ወንጌል፤ወደዚያ እንመለስም፤ነገር ግን ኢየሱስ በመንፈስ ተመርቶ ወደ ምድረ በዳ እንደወረደ ይናገራል፤ሆኖም በአርባኛው ቀን መጨረሻ ላይ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መጣ። እነዚያ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንደኛው ነገር በመንፈስ ቅዱስ መመራት ሲሆን፤ሌላኛው ነገር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሄድ እና መስራት ነው። ኢየሱስ ሰይጣንን ተዋግቶ ሳያሸንፈው ያንን አላደረገም።

በአንድ ደረጃ ወይም በሌላ፤ያ በእያንዳንዳችን ላይ የሚሆን ነው። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ለመንቀሳቀስ ፈተና እና ተግዳሮትን ማሸነፍ አለብን።

አሁን፤በማቴዎስ 4 ፈታኙ ወደ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፤የሰይጣን የመጀመሪያው ፈተና የነበረው ኢየሱስን እንዲጠራጠር ማድረግ ነበር። ያ በአብዛኛው ሰይጣን የሚጠቀምበት የመጀመሪያው አቀራረብ ነው። እሱ ወዲያውኑ የእግዚአብሔርን ቃል አይክድም፤ቃሉን እየጠቀሰ ይጠይቃል። እንድትጠራጠሩ ሊደርጋችሁ ይጥራል። ይህ ለበርካታ ጊዜ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ የሰራ ነው፤እሱ ሌላ ዘዴ ለማግኘት አልሞከረም፤ምክንያቱም ይህ ሁልጊዜ የሚሰራ ሆኖ አግኝቶታልና። ይህ በእናንተ ላይ እንዲሰራ አትፍቀዱ። እንግዲህ በማቴዎስ ምዕራፍ 4፤3 ላይ ሰይጣን ለኢየሱስ ያለውን የመጀመሪያው ነገር አስተውሉ፤

ፈታኝም ቀርቦ÷ የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ÷ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው። የሚል ነበር።

አሁን፤እግዚአብሔር ከሰማይ ይናገራል እንዲህም ይላል “የምወደው ልጄ እሱ ነው”፤ ሰይጣን ደግሞ ከእግዚአብሔር የሰማውን በመጠቀም “የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥ እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው።” በማለት ይጠይቃል።

እርሱም መልሶ፦ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።

በነገራችን ላይ፤ኢየሱስ ለሰይጣን የመለሳቸው ሦስቱም መልሶች ሁሉ ከዘዳግም መጽሐፍ የተወዱ መሆናቸው እጅግ አስደናቂ ነው። እንዲሁም ኢየሱስም ሆነ ሰይጣን የዘዳግምን መጽሐፍ ስልጣን አለመጠየቃቸው ደግሞ ሌላው የሚያስደንቅ ጉዳይ ነው። ስለዚህ፤ ለምን እየጠየቃችሁ ጊዜአችሁን ታባክናላችሁ?

እንግዲህ ኢየሱስ ፈተናን በዚህ መንገድ ነው የሚያስናግደው። ይህ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው። እሱ ፈተናን የሚያልፈው ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በመጥቀስ "ተብሎ ተጽፏል" በማለት ነው። ከሰይጣን ጋር ለመከራከር በጣም ብልህ ነኝ ብላችሁ አታስቡ፤ሰይጣን ከእናንተ ይልቅ በጣም ብልህ ነው። እሱ በዚህ ስራ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ኖሯል። በራሳችሁ የመከራከር ብቃት እሱን ለማሳመን አትሞክሩ፤ሰይጣንን የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ ግጠሙት። በእያንዳንዱ ጊዜ ኢየሱስ ሲፈተን፤ "ተብሎ ተጽፏል. . . ተብሎ ተጽፏል. . . ተብሎ ተጽፏል" በማለት ይመልስ ነበር። ኢየሱስ ይህን በሚልበት ጊዜ ሰይጣን ርዕሱን ይቀይር ነበር። እሱ ለመጽሐፍ ቅዱስ መልስ እንደሌለው ያውቃል። ስለዚህ ሰይጣንን በራሳችሁ ፍልስፍና ወይም የስነ መለኮት እውቀት ለመግጠም ስትሞክሩ ፈተና ውስጥ አትወደቁ። ነገር ግን ከተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል በመጥቀስ መልሱለት።

አያችሁ፤ኢየሱስ ሄዋን የሰራችውን ስህተት አልሰራም። በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 በሚገኘው ወደ መጀመሪያው የሰው ልጅ ታሪክ ስትመለሱ፤የመጀመሪያዎቹ ምንባቦች እንዲህ ይላሉ፤

እባብም እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠረው ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ ተንኰለኛ ነበረ። ሴቲቱንም፦ በውኑ እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ እንዳትበሉ አዝዞአልን? አላት።

መጀመሪያ ምን በማድረግ ፈተናት? እንድትጠራጠር በማድረግ፤ያ ትክክል ነው። በምትጠራጠሩ ጊዜ ቀጣዩ ደረጃ የሚሆነው አለማመን ከዛም አለመታዘዝ ነው። አስተውሉ፤ለጥርጣሬ ስፍራ መስጠት የለባችሁም።

ደህና፤ሔዋን በዲያቢሎስ ደረጃ ልትሆን እንደምትችል በማሰብ ስህተት ሰራች፤ስለዚህ "በገነት ካለው ከዛፍ ፍሬ እንበላለን፤" በማለት መልስ መለሰች፤ የህይወት ዛፍ ከሆነው "በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ በስተቀር፦" የሚለው ክልከላ እንደነበረባት እውቅና መስጠት አልፈለገችም። ያንን አስመልክቶ እንዲህ አለች፤ "ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፦ እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም።" የሰይጣን መልስ ምን እንደሆነ አስተውሉ፤ እባብም ለሴቲቱ አላት፦ ሞትን አትሞቱም፤

ለዚህ ነው የሚመጣው። እሱ ጥያቄ በመጠየቅ ይጀምራል፤ሆኖም ግን ወደ ክህደት ያመራል። ላለፉት መቶ ወይም ከዛ በላይ ለሆኑ ዓመታት የቤተክርስቲያንን ታሪክ ያጠናችሁ ከሆነ፤ሰይጣን የስነ መለኮት ተማሪዎችን ወይም ሰባኪያንን ወይም ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ የት ስፍራ ላይ እንዳታለላቸው ታገኛላችሁ፤ከመጽሐፍ ቅዱስ እየጠቀሰ ይጠይቃቸዋል፤ስለዚህ ሁልጊዜ በእርግጥ ወደሚክዱበት ነጥብ ያመጣቸው ነበር። በሚያንሸራትት ቁልቁል መንገድ አትጀምሩ። መጽሐፍ ቅዱስ ስልጣን አለው። የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ተቀበለው። ኦርበት። ለሰይጣን ከእግዚአብሔር ቃል ጠቅሳችሁ መልሱ። እሱ የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ቃል ሊከላከል አይችልምና።

በኤፌሶን 6፤17 ጳውሎስ እንዲህ ይላል፤

የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ስለ ቃል ሁለት የግሪክ ቃላት እንዳሉ ምናልባት ታውቁ ይሆናል።አንደኛው ሎጎስ ሲሆን፤ሌላው ሬማ ነው። ሎጎስ አጠቃላይ የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ምክር ሲሆን፤ሬማ ደግሞ በእግዚአብሔር የተነገረው የእግዚአብሔር ቃል ነው። የመንፈስን ሰይፍ መያዝ ተብሎ በኤፌሶን 6፡17 የተጠቀሰው ቃል ሬማ ነው። ዲያቢሎስን በምታገኙት ጊዜ፤የእግዚአብሔርን ቃል በመናገር ልትገጥሙት ያገባል።

መጽሐፍ ቅዱስን ሳታነቡት በመጽሐፍ መደርደሪያ ላይ ካደረጋችሁት ወይም በጠረጴዛችሁ አጠገብ እንኳን ካኖራችሁት ሊረዳችሁ አይችልም። የሚሰራው የጠቀሳችሁ ስትናገሩት ብቻ ነው። እንግዲህ ወደ አፋችሁ ወስዳችሁ ለራሳችሁ ስትናገሩት፤ስለታም እና የሚወጋ ቃል ይሆናል፤ዲያቢሎም ይሸሻል። ሰይጣን ለመጽሐፍ ቅዱስ መልስ የለውም።

አንግዲህ አሁን ኢየሱስ በጽሁፍ ስለተቀመጠው የእግዚአብሔር ቃል ስልጣን የተናገረውን እንመልከት። አስቀድሜ የተናገርኩትን ታስታውሳላችሁ? የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ማለት በጽሑፍ የተቀመጠ የእግዚአብሔር ቃል ማለት ነው። ኢየሱስ በማቴዎስ 5 ከቁጥር 17– 18: እንዲህ ይላል፤

“እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።”

ያ እኛ ብሉይ ኪዳን፤ህግ እና ነብያት ብለን የምንጠራው አይሁድ የሚናገሩበት መንገድ ነው።

እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።
እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።

እስቲ አሁን፤ጆት እና ቲትል የተባሉ ቃላትን እንመልከት። ጆት በዘመናዊ አብራይስጥ የሚገኝ ቃል ነው፤? ዮድ ? በአብራይስጥ ፊደል በጣም አነስተኛው ቃል ነው። እንዲሁም ቲትል ፊደልን ከተመሳሳይ ፊደል ለመለየት ከፊደሉ አናት ላይ የሚቀመጥ በትንሹ ቆልመም ያለ ነገር ነው። ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ጽሁፍ ውስጥ ያሉ ትናንሽ ነገሮች ናቸው። እንግዲህ ኢየሱስ ከእነርሱ ማንም አይጠፋም ይላል። ይህ እንግዲህ ኢየሱስ ለተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ስልጣን እውቅና እየሰጠ እንደሆነ በግልጽ የሚያመለክት ነው። እሱ በዚያ ነጥብ ላይ ስለተነገረው የእግዚአብሔር ቃል እየተናገረ አይደለም፤ምክንያቱም ጆት እና ቲትል የሚባሉት ቃላት የሚተገበሩት በጽሁፍ ላይ ብቻ መሆናቸው ነው። ስለዚህ ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ለተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ድጋፍ ሰጥቷል።

በማቴዎስ ምዕራፍ 22 ኢየሱስ የአገልግሎቱ ማብቂያ አከባቢ፤ የሁሉንም ቅዱሳን መጽሐፍት ስልጣን ካልተቀበሉት ሰዎች ጋር፤ማለትም ለዚያ ቀን ነጻ ሃሳብ ካላቸው ሰዱቃውያን ጋር እየተወያየ ነው። በእርግጥ፤የመጀመሪያዎቹን የአምስት መጽሐፍት ስልጣን ብቻ ወይም፤ፔንታቲዩክ የተባሉትን ተቀብለዋል። የሙታን ትንሳኤ አለ የሚለውን ትምህርት ይሞግቱ ነበር። ወደ ኢየሱስ አንድ ጥሩ የሆነ ጥያቄ ይዘው መጡ፤ነገር ግን የሚከተለው ምንባብ ኢየሱስ እንዴት እንደመለሰላቸው የሚያሳይ ነው፤ማቴዎስ 22፤31–32:

“ስለ ትንሣኤ ሙታን ግን፦ እኔ የአብርሃም አምላክ፥ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ የሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም።”

ኢየሱስ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት እንደተጠቀመ አስተውሉ። እነዚያ ቃላት ከአስራ አራት ከፍለ ዘመን በፊት በሙሴ የተነገሩ ነበሩ። በእርግጥ ቃሎቹ ለሙሴ በቀጥታ እግዚአብሔር የተናገራቸው ነበሩ። ዳሩ ግን ኢየሱስ ከአስራ አራት ክፍለ ዘመን በፊት እንደ ተራ ነገር ለሙሴ የተነገሩ ስለመሆናቸው አልተናገረም። ይህ በጣም አይለኛ ቃል ነው። እንዲህ አለ “ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን?” አያችሁ? የእግዚአብሔር ቃል አያረጅም። ይህ በሰው ልጅ ብልህነት የተመዘገበ አይደለም፤በእግዚአብሔር አዋቂነት እንጂ። ከሦስት ሺ አመታት በፊት የተጻፈ ቢሆንም ቅሉ ዛሬም ግን እየተናገራችሁ ነው። ያ ኢየሱስ እንደተረዳው የእግዚአብሔር ቃል ስልጣን ነውና።

አሁን የኢየሱስ ህይወት የተጻፈውን የእግዚአብሔር ቃል እንዴት እንደፈጸመ መመልከት ያስፈልገናል። አዲስ ኪዳንን የምታጠኑ ከሆነ በኢየሱስ ህይወት ውስጥ አንድ ነገር ሲከናወን “ቃሉ ይፈጸም ዘንድ ነው” የሚል አስራ ስምንት የተለያየ ቦታ ላይ ተጽፎ ታገኛላችሁ።በሌላ አባባል፤ኢየሱስ እንዲያው ዝም ብሎ የእግዚአብሔርን ቃል ያመነ፤ወይም መጽሐፍ ቅዱስን እየጠቀሰ የተናገረ ብቻ ሳይሆን፤ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ በተግባር አሳይቷል። በመላ

ህይወቱ ላይ የእግዚአብሔር ቃል ይሰራ ነበር።

የእነርሱን ልዩ ልዩ የህይወት ገጽታዎች መውሰድ ትችላላችሁ፤ነገር ግን አኛ አራቱን ወስደን እንመለከታለን።ልደቱን፤ሰብአዊ ህይወቱን፤ሞቱን እና ትንሳኤውን። ሁሉንም አስመልክቶ፤መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤መጽሐፍ ይፈጸም ዘንድ እንዲህ ሆነ። ኢየሱስ ከዚያ በላይ አጥብቆ የመጽሐፍ ቅዱስን ስልጣን ይደግፋል።

አሁን ወደ አዲስ ኪዳን እንዙር። ከአዲስ ኪዳን ጀርባ ያለው ስልጣን ምንድ ነው? ኩበሉይ ኪዳን ጀርባ ካለው ስልጣን ጋር ተመሳሳይ መሆን ስታውቁ ትገረማላችሁ። እስቲ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ የተናገራቸውን ሁለቱን ምንባቦች እንመለከት። በዮሐንስ 14፤ቁጥር 25-26፤ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ትቷቸው ሊሄድ ነው፤እሱ ለሚሄድበት ዓላማ እየተዘጋጀ ነው፤እንዲህ ይላል፡

“ከእናንተ ዘንድ ስኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ፤”

ያ የመንፈስ ቅዱስ ስም ነው። ረዳት ነው። አንዳንድ ጊዜ አጽናኝ ተብሎ ይጠራል።

“አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።”

ስለዚህ ከሐዋሪያት መጻህፍት ጀርባ ያለው ስልጣን የመንፈስ ቅዱስ ስልጣን ነው። ኢየሱስ ሁለት ነገሮችን እንደሚያደርግ ይናገራል፤ እኔ ያላስተማርኳችሁን ሁሉ፤እሱ ያስተምራችኋል፤አንዲሁም እኔ ነግሬአችሁ የረሳችሁትን ሁሉ እሱ ያስታውሳችኋል። ስለዚህ የወንጌላት መዝገብ በሰው ልጅ የማስታወስ ችሎታ ላይ የተመሰረተ አይደለም፤በመንፈስ ቅዱስ እውነት ላይ የተመሰረተ እንጂ።

እንደገና፤ዮሐ 16፤12-14፤ ተመሳሳይ ነገር ይናገራል።ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸው፤

“የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ÷ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም።
ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ . . .”

እስቲ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ ነገር ገላጭ ሳይሆን ስብዕና ገላጭ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶ በመናገር የሰዋሰውን ህግ የሻረበትን ልጠቁም። ወደዚያ መግባት አልችልም ምክንያቱም በጣም የተወሳሰበ ነው፤ነገር ግን እንደ ግሪኩ ሰዋሰው መሰረት እርሱ (ሰው ላልሆነ ነገር) ማለት ነበረበት። ሆኖም እንደዛ አልተናገረም፤ ዳሩ ግን እሱ የገለጸው የስብዕና ገላጭ የሆነውን እሱን ነው። በሌላ አነጋገር፤እባክዎ መንፈስ ቅዱስ ስዕብና እንጂ ስዕብና ባልሆነ ነገር እንደማይገለጽ ተረዱ።

እሱ እሱ ነው፤እሱ ስዕበና ነው። እሱን እንደ ስዕበና አድርጋችሁ ልታውቁት ያስፈልጋል።

“ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።”

ስለዚህ እንደገና ኢየሱስ ይናገራል፤ልትማሩት የሚገባ፤ነገር ግን ገና ያልተቀበላችሁት ትምህርት፤በመንፈሰ ቅዱስ ወደ እናንተ ይመጣል።

እንዲህ ይላል፤

“የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።”

በሚቀጥለው ቁጥር ላይ እንዲህ ይላል፤

“እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና።”

ሌላኛውን በጣም አስፈላጊ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ምልክት ደግሞ ልንገራችሁ፤እሱ ኢየሱስን ያከብራል። ኢየሱስን የማያከብር ነገር ግን ለሰው ብቻ ክብር የሚሰጥ ወይም ወደ ሌላ አቅጣጫ የሚሄድ ማንኛውም አይነት መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ካጋጠሚችሁ ያ ከመንፈስ ቅዱስ እንዳልሆነ እርግጠኛ መሆን ትችላላችሁ። ምክንያቱም ትልቁ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ኢየሱስን መግለጥ እና ማክበር ነውና። ያ መናፍስትን የምንመረምርበት ጥሩ መንገድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መናፍስትን ሁሉ መለየት እንዳለብን ይናገራል። አንድ ነገር ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ መመርመር እንችላለን። አንድ አገልግሎት ከመንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እና እንዳልሆነ የምንመረምርበት አንዱ እርግጠኛ የሆነው መንገድ ያ አገልግሎት ኢየሱስን ማክበሩ ነው። እንደዛ የማያደርግ ከሆነ—በጣም ጥሩ ሊመስል ይችላል፤ወይም መንፈሳዊ ሊመስል ይችላል፤በጣም ሊጨህ ይችላል፤ከፍተኛ የሆነ ድምጽ ሊያሰማ ይችላል፤ሆኖም ያ ከመንፈስ ቅዱስ የመጣ አይደለም፤ምክንያቱም እሱ የሚከብረው ማንንም ሳይሆን ኢየሱስን ነውና። ሰዎች ክብርን ለራሳቸው መውሰድ በጀመሩበት ቅጽበት መንፈስ ቅዱስ “አዝናለሁ፤ነገር ግን መሄድ አለብኝ። አንተ መቀጠል ትችላለህ ነገር ግን እኔ እዚህ አልሆንም።” ይላል።ለዚህ ነው በርካታ በጣም በርካታ የሆኑ አገልግሎቶች ተበትነው መቅረታቸው የየዕለት ትውስታችን የሚሆኑት. . . አዎ የእለት ትውስታዎቻችን ናቸው፤ከአንዳንዶቻችሁ ይልቅ በጣም ይሰፋሉ። በብዙ መመሰቃቀል ደግሞ ወደ ፍጻሜአቸው የደረሱ በርካታ አገልግሎቶችን መቁጠር አልችልም፤ምክንያቱም ሰዎቹ መንፈስ ቅዱስ ለኢየሱስ የሚሰጠውን ክብር ለራሳቸው የሚወስዱ ስለሆነ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ በጣም በጣም ለራሴ እንደምጠነቀቅ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። እኔ ክብር እየሰጠሁ ያለሁት ለኢየሱስ ነው ወይም ሰዎችን ዴሪክ ፕሪንስ በጣም ጠቃሚው ሰው ነው?” እያልኩ ለማሳመን እሞክራለሁ። ዴሪክ ፕሪንስ በእግዚአብሔር ጸጋ የዳነ ሐጢያተኛ ሰው ነው።

አሁን፤በእውነት አስደናቂ እና አስፈላጊ ወደሆነው ርዕስ እንሂድ፤ያም የእግዚአብሔር ቃል ባህሪ ነው። ይህ በጣም በጣም አስደናቂ ነው። በዕብራውያን ምዕራፍ 4፤12 ስለ እግዚአብሔር ቃል ባህሪ የተለያየ አይነት ትንተናዎችን እናገኛለን።

የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና÷ የሚሠራም÷ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው÷. . .

እዚህ ጋር ከሰይፍ ጋር ሲነጻጸር ትመለከታላቸሁ

. . . ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል÷ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤

ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል አልሞተም፤በነጭ ወረቀት ላይ የሰፈሩ ጥቁር ምልክቶችም አይደለም፤ከሰባኪ አንደበት የሚወጣ ድምጽም አይደለም፤ህያው ነው፤የሚሰራም፤ከየትም ስፍራ ቢመጣ ህይወት የሚሰጥ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ህያውና ኃይለኛ ነው። ሰይጣን ዓለምን ከሞላው ውሸቶች ሁሉ ይልቅ ኃይለኛ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የመጨረሻ መልስ ነው።

እናም እንዲህ ይላል

. . . ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል. . .

ይህ እጅግ አስደሳች ነው። ነገር ግን፤መጽሐፍ ቅዱስ ሰው የሦስት ውህድ ፍጡር እንደሆነ ይናገራል፤መንፈስ፤ነፍስ እና ስጋ—የሦስት ውህድ ፍጡር የሆነው ሰው በስላሴ እግዚአብሔር ሃምሳል ተፈጥሯል፤ አብ፤ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ። ዳሩ ግን መንፈስ እና ነፍስን እንለይ ዘንድ ልንማር የምንችልበት ብቸኛው መንገድ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስጋዊ የሆነውን መንፈሳዊ ከሆነው የሚለይ እና የሚወጋው ብቸኛው ስለታም መሳሪያ ነው። ይህ በጣም አስፈላጊ ነው፤ምክንያቱም አዲስ ኪዳንን የምታጠኑ ከሆነ፤አሁን በእርግጥ አሁን ወደዚያ ለመግባት ጊዜ የለንም፤ነገር ግን ስጋዊ የሆነ ነገር በብዙ መንገዶች መንፈሳዊ በሆነው ላይ ሲነሳ እናገኛለን። በ1ኛ ቆሮ ምዕራፍ 2 ጳውሎስ ስጋዊ ሰው ከእግዚአብሔር መንፈስ የሆኑትን ነገሮች አይቀበልም ይላል፤ እነርሱ በመንፈስ የተለዩ ናቸው። ስለዚህ ስጋዊ የሆነውን መንፈሳዊ ከሆነው ለመለየት መማር በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ነገር ግን ያንን ሊያደርግ የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ነው።

ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም መለየት ደግሞ ይችላል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የዶክተር ኦፕራሲዮን ማድረጊያ ስለት በማያስፈልግበት መውጋት ይችላል፤እንዲሁም ያሳይካትሪስት ህክምና ሳያስፈልግ

መመረመር ይችላል። በጣም ጥልቅ ወደሆነው የሰው ስዕብና የሚወስደን የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው።

እናም እንዲህ ይላል፡

. . . የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራልና

መለየት ማለት መተንተን ማለት ነው፤የአንድን ነገር ተፈጥሮ በጥልቀት መመልከት ነው። ከዓመታት በፊት አዲስ አማኝ በነበርኩበት ወቅት፤አንድ ሰው "አስታውስ፤መጽሐፍ ቅዱስህን በምታነብ ጊዜ፤መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ አንተን ያነብሃል።"ብሎ የተናገረኝን ሁልጊዜ ሳስታውሰው እኖራለሁ። የሁለት አቅጣጫ ልውውጥ ነው። ለእኔ በጣም ግልጽ ነበር፣ምክንያቱም እኔ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ስጀምር የእግዚአብሔር ሥራ አድርጎ እንደሚመለከት እንደ አንድ የፍልስፍና ባለሙያ ነበር። ነገር ግን ማንበብ እንደጀመርኩ፤በጣም አሰልቺ ሆኖ አገኘሁት፤እና የእኔ ብቸኛ ሃሳብ የነበረው ምንም አይነት መጽሐፍ አሸንፎኝ እንዳነበው አድርጎኝ አያውቅም የሚል ነበር፤ስለራሴ በጣም የተለየ ነገር ይሰማኝ ጀመር። በዚያን ጊዜ በእውነት ለሁሉም ነገር መልስ እንዳገኘሁ አሰብኩ። ፍልስፍና ለሁሉም ነገር መልስ መስጠት ይችላል፤ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ በቀጠልኩ ጊዜ በጣም ዝቅተኛ እና ዝቅተኛ የሆነ በራስ መተማመን ተሰማኝ። በእኔ ላይ እየሆነ የነበረውን ነገር መረዳት አልቻልኩም ነበር። በዚያ ጊዜ ሃያ አምስት ዓመት እንኳን ያልሞላኝ ወጣት ብሆንም፤ነገር ግን ከእድሜ ቀድሜ እያረጀሁ ነው ብዬ አስብ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ በማነብበት ጊዜ፤መጽሐፍ ቅዱስ ግን ራሴን ያነበኝ እንደነበር አልተገነዘብኩም ነበር። በስተመጨረሻም ብልጣሶር በራሱ ድግስ ወቅት፤በግድግዳው ላይ "በሚዛን ተመዝነህ ቀለህ ተገኘህ" የሚለው በታየ ጊዜ እንደሆነው ተሰማኝ። እና በራስ መተማመኔ፤ኩራቴ፤ትዕቢቴ፤የአዕምሮዬ የማሰብ ችሎታዬ ሁሉም በመጽሐፍ ቅዱስ ፊት መቅለጥ ጀመረ። ይሁንና በዚያን ጊዜ አላመንኩም ነበር—ነገር ግን ስራውን አሁንም እየሰራ ነበር። ስለዚህ ያንን በአዕምሯችሁ ያዙ፤መጽሐፍ ቅዱስን በምታነብቡ ጊዜ፤መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ እናንተን ያነባችኋልና።

አሁን እስቲ ለአንድ ተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሚያደርገው አሰራር እይታ ወደ 1ኛ ተሰሎንቄ ለአፍታ እንመለስ። 1ኛ ተሰሎንቄ 2፤13። ጳውሎስ ለወንጌል መልዕክት አስደናቂ በሆነ መንገድ ምላሽ ለሰጡ በተሰሎንቄ ላሉ አማኞች እየጻፈ ነው። እናም እንዲህ ይላል፤

> ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ÷ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት÷ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን።

መጽሐፍ ቅዱስ በእናንተ ህይወት የሚሰራው በተቀበላችሁት መጠን እንደሆነ ትረዳላችሁ። እንደ ሰው መጽሐፍ

የተቀበላችሁት ከሆነ፤ሙሉ ስራውን በእናንተ አይሰራም። ዳሩ ግን፤ እንደ እግዚአብሔር ቃል ከተቀበላችሁት ውጤታማ በሆነ ሁኔታ በእናንተ ይሰራል።

እንዲሁም፤መጽሐፍ ቅዱሳችሁን በምታነቡ ጊዜ፤አሁን ጊዜ ውሰዱና ለጌታ እንዲህ በሉት "በዚህ በቃል የተጻፈውን አምናለሁ። የአንተ ቃል እንደሆነ እቀበላለሁ፤አንተ በሕይወቴ እንዲሰራ የላከውን ሁሉ፤በየትኛውም የህይወቴ ክፍል—መንፈስ፤ነፍሴ እና ስጋዬ—ላይ ይስራ፤ምክንያቱም በቃልህ አምናለሁና።"

ጴጥሮስ በ2ኛ ጴጥሮስ 1 ላይ ያስቀመጠውን አስደናቂ ምንባብ መመልከት ያስፈልገናል፤እጅግ አስደናቂ ከሆኑ ጥቅሶች አንዱ ነው፤መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉ ጥቅሶች አንዱ እንደሆነ አስባለሁ። 2ኛ ጴጥሮስ 1፤3 እና 4። በዓረፍተ ነገረ መካከል ያለ ነው። ሐዋሪያት ረዘም ያለ ዓረፍተ ነገሮችን ጽፈዋል። ጳውሎስ ረጅሙን እንደጻፈ አስባለሁ ነገር ግን ጴጥሮስም ረዘም ያለ ጽፏል። በኢንግሊዝኛው ልንከፍላቸው ይገባል። ወደዚህ የዚህ ዓፍተ ነገር መጀመሪያ አልመለስም፤ከመካከል እጀምራለሁ።

የመለኮቱ ኃይል፥ በገዛ ክብሩና በበጎነቱ የጠራንን በማወቅ፥ ለሕይወትና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚሆነውን ነገር ሁሉ ስለ ሰጠን፥ በእግዚአብሔርና በጌታችን በኢየሱስ እውቀት ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።

ያ አስደናቂ ምንባብ ነው። የእግዚአብሔር መለኮት፤ምንም የማይሳነው ኃይሉ የሚስፈልገንን ሁሉንም ነገሮችን ሰጥቶናል! ይላል። "ደህና፤እግዚአብሔር ሆይ፤የማገኘው አይመስለኝም፤የት ነው ያለው?" ብላችሁ ትመልሱ ይሆናል። ቀጣዩ ጥቅስ ይነግረናል፤

ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተስፋ ቃል እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ ታላቅ የሆነ ተስፋን ሰጠን።

እንግዲህ እግዚአብሔር ለህይወት እና እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያስፈልገንን ሁሉ አንዴት ነው የሰጠን? እነሱ የሚገኙትስ የት ነው? እነሱ የሚገኙት በተስፋ ቃሎች ውስጥ ነው። "አቅርቦቱ ያለው በተሰጠው የተስፋ ቃሎች ውስጥ ነው።" ብዬ ያዘጋጀሁትን ትንሽ ዓረፍተ ነገር እወደዋለሁ። ስለዚህ "አቅርቦቱ ያለው በተሰጠው የተስፋ ቃሎች ውስጥ ነው።" የሚለውን ዓረፍተ ነገር አብራችሁን ልትሉ ትወዳላችሁን? እንግዲህ እግዚአብሔር ለእናንተ ያቀረበውን መቀበል ከፈለጋችሁ፤በሰጠው የተስፋ ቃሎች ውስጥ መቀበል አለባችሁ ምክንያቱም በተስፋ ቃሎች ውስጥ የሚያስፈልጓችሁ ሁሉ ተዘጋጅተዋልና።

የሚመጣውም ኢየሱስን በማወቅ ነው፤ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን ይገልጠዋልና። አስገራሚ ምንባብ ነው—ይህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተጽፎ ያልተቀመጠ ቢሆን ኖሮ አልናገረውም ነበር—ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት አምልጠን የመጣን፤የተስፋ ቃል ተካፋዮች በመሆን የመለኮቱ ባህሪ ተካፋይ መሆን እንችላለን።

አሁን፤በጣም መጠንቀቅ ይኖርብናል፤ምክንያቱም የማልጠቅሰው የትምህርት ዓይነት አለ፤ነገር ግን አብዛኞቻችሁ

ስሙን ታውቁታላችሁ፤በዚህ ጊዜ በጣም ተወዳጅ የሆነ ነው፤ያም ብዙ ከተጓዛችሁ፤እና መልካም ነገሮችን የምታደርጉ ከሆነ አማልክት መሆን ትችላላችሁ በማለት ያስተምራል። አንዳንዶቻችሁ ያንን ትምህርት እንዳገኛችሁ እርግጠኛ ነኝ። በእርግጥ፤ የአዲሱ ዘመን (New Age) በመባል ይታወቃል። አዲሱ ዘመን የሚለውን ሃረግ እጠቀም ነበር፤አዲሱ ዘመን እየመጣ ነው በማለት እናገር ነበር። እንግዲህ ከእኔ ሰርቀዋል፤ስለዚህ ሌላ ነገር ማሰብ ይኖርብኛል ማለት ነው! የእግዚአብሔር መንግስት በምድር ላይ ሊመሰረት ነው አያልኩ እናገር ነበር። እነርሱ የማይፈልጉት—ኢየሱስ መንግስቱን ሊመርት ነው!

ነገር ግን ለማንኛውም፤አዲሱ ዘመን፤በአብዛኛው ከሂንዱ ፍልስፍና ጋር የተዛመደ ነው ስለሆነም፤በደንብ ከተጓዛችሁ—በማለት ያስተምራል።በነገራችን ላይ ሞርሞኖችም የሚስተምሩት ተመሳሳዩን ነው። እነሱ በመጀመሪያ በአደባባይ አይናገሩትም፤ነገር ግን—አምላክ መሆን ትችላለህ የሚለው ትምህርት በእነሱ ዘንድ ነው። ያ በግልጽ ሐሰት እንደሆነ ልነግራችሁ እወዳለሁ፤እናም አንድ መሰረታዊ ምክንያት እነግራችኋለሁ። እግዚአብሔር ፍጥረት አይደለም፤እኛ ግን ፍጥረቶች ነን። ፍጡር መቼም ፈጣሪ ሊሆን አይችልም። ያ ማሳሳት ነው። ነገር ግን የተስፋ ቃሎችን ስንቀበል እና ተግባራዊ ስናደርግ የእሱ መለኮታዊ ባህሪ ተካፋይ መሆን እንችላለን።

እኔ ሁልጊዜ ስለ ያዕቆብ መሰላል አስባለሁ። እሱ ያለመውን ህልም ምናልባት ታስታውሱ ይሆናል። እሱ በምድረበዳ ውስጥ ነበር፤እናም ድንጋይን ተተርሶ ተኛ። ስንቶቻችሁ ድንጋይን ለትራስነት ተጠቅማችሁ ታውቃላችሁ? አብዛኞቻችሁ ተመችቷችሁ አትጠቀሙበትም። ነገር ግን ያዕቆብን ድንጋይን ተተርሶ ተኝቶ ነበር። በአንድ ወቅት አንድ ሰው “ያዕቆብ ያለመውን ህልም ማየት የምችል ከሆነ ድንጋይ ተተርሶ ለመተኛት ፈቃደኛ ነኝ!” ሲል ሰምቸዋለሁ። ምክንያቱም እሱ ከተመለከተው ራዕይ የተነሳ ነው፤ከምድር ሰማይ የሚደርስ መሰላልን የሚያሳይ ህልም። እግሩ መሬት ላይ ሲሆን፤የመሰላሉ ጫፍ ግን ሰማይ ይደርስ ነበር፤በዚያም የእግዚአብሔር መላዕክት ይወጡ እና ይወርዱ ነበር። ኢየሱስ ራሱ በመሰላሉ ጫፍ ላይ ሆኖ ይናገር ነበር።

በያዕቆብ መሰላል ስሜት ውስጥ ሆኜ መጽሐፍ ቅዱስን አስባለሁ። አያችሁ፤እያንዳንዱ የተስፋ ቃል የመሰላል አንድ ደረጃ ነው። በየጊዜው ወደ አንድ ከፍታ ስትወጡ ተገቢ የሆነ አዲስ የተስፋ ቃል አለ።በመጨረሻም ወደ ሰማይ ይወስዳችኋል። መጽሐፍ ቅዱስ ለእናንተ መልካም የሆነ ህይወት ቁልፍ ስለሆነ ችላ ልትሉ አይገባም። ለስኬትዎ ቁልፍ ነው። እግዚአብሔር የሰጠን እጅግ የከበረ ስጦታ ነው።

ዛሬ ብዙ አይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እንዳሉን ልብ ይሏል፤እንግዲህ የትኛውን ትረጉም መጠቀም እንዳለብን ውይይት እናደርጋለን፤በምሳሌ ወይም በማስታወሻ ልናቀርብ እንወዳለን፤በዓለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር መጽሐፍ ቅዱሰን ገልጠው የማያውቁ ሰዎች መኖራቸውን አስታውሱ። እነሱ ምንም ምርጫ የላቸውም። እስቲ ያለፉ ታሪክ

ቢሆንም፤ሌላም ነገር እናስታውስ። ባለፈው ክፍለ ዘመናት፤መጽሐፍ ቅዱስን ለእኔ እና ለእናንተ ጠበቆ ለማስተላለፍ ህይወታቸውን በመስዋዕትነት ያቀረቡ ወንዶች እና ሴቶች ልጆች መኖራቸውን እናስታውሱ። ስለዚህ በክብር እንቀበለው። ለመጽሐፍ ቅዱስ ክብር እናሳይ ምክንያቱም እግዚአብሔር ወደ ህይወታችን የሚመጣበት መንገድ ነውና።

አሁን ይህንን ክፍል አንድ የሚያስደንቅ ነገር በመናገር ልዘጋው እወዳለሁ።ይህ የእግዚአብሔር ቃል ውጤት ነው። ጳውሎስ ቃሉን ስላመናችሁ በህይወታችሁ በውጤታማነት ይሰራል ብሎ ለተሰሎንቄ ሰዎች ይናገራል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል በህይወታችሁ የሚኖረውን ስምንት ውጤቶች ልጠቅስ እወዳለሁ። እነዚህ ነገሮች የእግዚአብሔር ቃል በእኔ እና በእናንተ ህይወት የሚሰራቸው ናቸው።

መጀመሪያ ወደ ሮሜ ምዕራፍ 10፤17

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።

እንግዲህ ይህ በጣም አስደናቂ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ነው፤ምክንያቱም በቆዳ በሽታ ምክንያት በሰሜን አፍሪካ በረሃ በሚገኝ በአንድ ሆስፒታል ውስጥ ለአንድ ዓመት ተኝቼ ነበር፤ዶክተሮች በዚያ የአየር ንብርት ምክንያት ሊያድኑኝ አልቻሉም ነበር። ከዚያም እየዋለ እያደር ክሮኒክ ኤክስማ ወይም ስር የሰደደ ችፌ ብለው ወደ ሚጠሩት አደገ። በእውነቱ፤ለዚህ ዓይነት በሽታ ዛሬም ቢሆን ፈውስ አላገኙለትም። ስለሆነም አዲስ ክርስቲያን እንደመሆኔ መጠን ለራሴ "እምነት ቢኖረኝ እግዚአብሔር እንደሚፈውሰኝ አምናለሁ" እል ነበር።ነገር ግን ሁልጊዜ እናገር የነበረው ቀጣዩ ነገር ፤ "ነገር ግን አምነት የለኝም" የሚል ነበር። ሆኖም ጆን ቡንያን ተስፋ የመቁረጥ ረግረጋማ ስፍራ፤ተስፋ የመቁረጥ ሸለቆ ብሎ በጠራው ውስጥ ነበርኩ።

እናም ከለታት አንድ ቀን ብሩህ የሆነ የብርሃን ጨረር በዚያ የጨለማ ሸለቆ ውስጥ በራ እናም ከሮሜ 10፤17 መጣ፤

እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው . . .በማለት፤

እምነት ከሌላችሁ፤ማግኘት ትችላላችሁ። ያለ እምነት መኖር የለባችሁም። እምነት የሚመጣው

የእግዚአብሔርን ቃል ከመስማት ነው።

እንግዲህ እምነት አሁን እዚህ ሆናችሁ የእግዚአብሔርን ቃል እየሰማችሁ ሳላችሁ ወደ አብዛኞቻችሁ እየመጣ ነው። እንደምታውቁት

በአዲስ ኪዳን ሰዎች በሚያነቡ ጊዜ ፤የሚያነቡት ለራሳቸው ብቻ እንኳን ቢሆን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ነው። ለምሳሌ፤ኢትዮጲያዊው

ጃንደረባ በሰረገላው ላይ ሆኖ የነብዩ ኢሳያስን መጽሐፍ ለራሱ እያነበበ የነበረ ቢሆንም፤ፊሊጶስ ሲያነብ ሰምቶት ነበር። ድምጽን ከፍ

አድርጎ በማንበብ አንድ የሚሆን ነገር አለ። ምክንያቱም እያነበባችሁ እራሳችሁን ስትሰሙት እምነት ይመጣል፤አያችሁ?

ደህና፤ያ ቁጥር አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ውጤት ነው።

ቁጥር ሁለት አዲስ ውልደት ይሰጣል። እኛ ዳግምኛ የተወለድነው በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት ነው።

ያዕቆብ ምዕራፍ 1፤18 እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

ለፍጥረቱ የበኵራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል *[መጽሐፍ ቅዱስን]* አስቦ ወለደን።

ለምን እግዚአብሔር እንደዚህ እንዳደረገ ታውቃላችሁ? ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊያደርገው ወስኗልና። ከዚያ ያለፈ ምንም ተጨማሪ ማብራሪያ አይኖረንም። ወደ ማንኛውም ነገር መጀመሪያ ስትመሰርቱ፤ሁሉም የጀመሩት በእግዚአብሔር ውሳኔ ነው። እግዚአብሔር ህዝቡን ወደራሱ ለማምጣት ወሰነ፤ስለሆነም በእግዚአብሔር ቃል፤በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ለመምጣት ወሰነ።ለዚያም ነው አዲስ ፍጥረት ለመሆን፤የእግዚአብሔር ህዝብ ለመሆን፤እግዚአብሔርን ወደማወቅ በእግዚአብሔር ቃል ያመጣችሁ።

እንግዲህ 1ኛ ጴጥሮስ ወደ ተመሳሳይ ርዕስ ይሄዳል። 1ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 1፤22-23፤

ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደድ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ

ነፍሳችሁን እንዴት እንደምታነጹ አስተዋላችሁ? ለእውነት በመታዘዝ ነው። ቃሉን በመስማት ብቻ ሳይሆን፤ነገር ግን በመታዘዝ ነው።

እናም ውጤቱ ምን ይሆናል? ውጤቱ የጠለቀ ፍቅር ነው።

እናም ጴጥሮስ ይቀጥላል፡

. . .ዳግምኛ የተወለዳችሁት. . .

. “ዳግምኛ የተወለዳችሁት” የሚለውን አስተውሉ

. . . ከሚጠፋ ዘር አይደለም ነገር ግን ከማይጠፋ ዘር ነው።

የማይጠፋ ዘር ምንድ ነው?

. . . በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።

.

ስለዚህ በእምነት ወደ ልብ የገባው እና አዲስ ልደት የሚሰጠው የእግዚአብሔር ቃል ዘር ነው።ዘሩ የማይጠፋ ነው፤የሚያመጣውም ህይወት የማይጠፋ ነው። የዘሩ ባህሪ የሚመጣውን ህይወት ባህሪ ይወስናል። የፖምን ዘር ተክላችሁ የብረቱካንን ዛፍ ልታገኙ አትችሉም። የዘሩ ተፈጥሮ የሚመጣውን ህይወት ተፈጥሮ ይወስናል። የእግዚአብሔር ቃል የማይጠፋ ነው፤ከዚያም የሚመጣው ህይወት የማይጠፋ ነው። መለኮታዊ ነው፤ቅዱስ ነው፤ዘለዓለማዊ ነው።

አንዴ ዳግም ከተወለዳችሁ በኋላ የሚያስፈልጋችሁ ምግብ ነው። የሚያስደንቀው ነገር የእግዚአብሔር ቃል በማንኛውም የመንፈሳዊ እድገት ላይ ላለ ሁሉ ተስማሚ የሆነ ምግብ አቅርቧል። መንፈሳዊ ህጻን ከሆናችሁ የሚያስፈልጋችሁ ወተት ነው፤ያም ጴጥሮስ በ1ኛ ጴጥሮስ 2፤2 የሚናገረው ነው፤

> ጌታ ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እንደ ሆነ÷ ለመዳን በእርሱ እንድታድጉ አሁን እንደ ተወለዱ ሕፃናት ተንኰል የሌለበትን የቃልን ወተት ተመኙ።

ስለዚህ አንዴ ዳግም ከተወለዳችሁ ለእግዚአብሔር ቃል ጤናማ የሆነ ረሃብ ሊኖራችሁ ይገባል። እርግጠኛ ነኝ፤ዛሬ በዚህ ምሽት ይህን የእግዚአብሔርን ቃል የተራባችሁ ትኖራላችሁ፤ዳግምኛ በተወልንበት ጊዜ የምንፈልገው ነገር የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ ብቻ እንደነበር መመስከር እንችላለን። በእውነት ሊመግበን ለሚችል ጤናማ የሆነ የምግብ ፍላጎት ያለን ህጻናት ሆነን ተወልደናል።

ነገር ግን በምናድግበት ጊዜ እንደ ዳቦ አይነት ምግቦች ያስፈልጉናል። ይሁን እንጂ ወደዚያ መዞር የለብንም፤ሰይጣን ድንጋይን ወደ ዳቦ እንዲቀይር በፈተነው ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ምላሽ ሰጥቶ ነበር፤

“ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው።”

ስለዚህ፤የእግዚአብሔር ቃል ወተት ብቻ ሳይሆን፤ዳቦም ነው።

ነገር ግን እያደግን ስንሄድ ተጨማሪ ጠጣር ምግቦች ያስፈልጉናል፤ይህ ደግሞ የተዘጋጀ ነው። በዕብራውያን ምዕራፍ 5 የዕብራውያን ጸሃፊ

ከመጀመሪያውም የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት ለነበራቸው ለአይሁድ ሰዎች እየጻፈ ነው። እግዚአብሔር ለእንዳንዶቻችን ሊናገር

የሚፈልገውን እየነገራቸው ነው፤“ሁሉንም ስለምታውቁ፤አሁን ካላችሁበት በተሻለ ማደግ ነበረባችሁ።” እንዲህም አላቸው “የመጽሐፍ

ቅዱስን እውቀት አግኝታችኋል፤ነገር ግን እየተጠቀማችሁበት አይደለም።” እስቲ እነዚህን ቃላትን ከዕብራውያን 5፤12 ላይ ላንብብላችሁ፤

ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ÷ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም።

ማስረጃው ምንድ ነበር? በጣም ቀላል የሆነውን እና መሰረታዊ የሆኑ እውነቶችን እንኳን አላምጠው መዋጥ አልቻሉም ነበር።

ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤
ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በስራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።

ተረዳችሁ? ለማደግ ስሜቶቻችሁን ማሰራት አለባችሁ። ልምምድ ማድረግ አለባችሁ። የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ ማድረግ አለባችሁ፤ያላችሁበትን ሁኔታ ለማወቅ እንዲሁም እየተዋጋችሁ ያላችሁትን ሃይላት ለመረዳት መጠቀም አለባችሁ። ወደ እድገት የሚወስደው መንገድ ይህ ነው። በእውነት የእግዚአብሔርን ቃል ተግባራዊ የማታደርጉ ከሆነ፤በእግዚአብሔር ቃል የማትኖሩ ከሆነ፤መቼም አታድጉም፤ከወተት ያለፈ ነገር ልትወስዱ አትችሉም ወይም ምናልባት ትንሽ ዳቦ ትወስዱ ይሆናል። ዳሩ ግን ጠጣር ምግብ የሚያስፈልገው ለሚሰሩ፤ለሚለማመዱ፤በትጋት ሁልጊዜ በህይወታቸው ተግባራዊ ለሚያደርጉ ነው።

ስለዚህ ያ ሦስተኛው እግዚአብሔር ቃል ውጤት ነው፤መንፈሳዊ ምግብ ነው።

አራተኛው ውጤት የአዕምሮ ብርሃን ነው። ወደ መዝሙር 119 መመለስ እፈልጋለሁ፤እርግጠኛ ነኝ ብዙዎች የሚያውቁት ጥቅስ ነው። መዝሙር 119፤130። ዘማሪው ለእግዚአብሔር ይናገራል እናም እንዲህ ይላል

የቃልህ ፍቺ ያበራል÷ ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።

ስለዚህ፤የእግዚአብሔር ቃል ፍቺ ለአዕምሯችን እና ልባችን ብርሃን ይሰጣል። ከመደበኛ ትምህርት ከምናገኘው የተለየ ነው። መደበኛ ትምህርት ብርሃን አይደለም። የተማራችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ ሆኖም ግን ፍጹም በሆነ ጭለማ ውስጥ ልትኖሩ ትችላላችሁ። ይህን የማውቀው እንዴት ነው? ምክንያቱም በዚያ ነበርኩና። እኔ በጣም የተማርኩ ነገር

ግን የእግዚአብሔር ቃል በህይወቴ ላይ እስኪያበራ ድረስ ድቅድቅ በሆነ ጨለማ ውስጥ ነበርኩኝ። ስለዚህ መደበኛ ትምህርት ብርሃን አንዳልሆነ አስተውሉ።

ከዓመታት በፊት፤ትምህርትን ለማግኘት ትልቅ መሻት ከነበራቸው ከአፍሪካውያን ተማሪዎች ጋር በምስራቅ አፍሪካ እነጋገር ነበር። "ትምህርትን እየፈለጋችሁ ነው ነገር ግን ጥበብን እያገኛችሁ ነውን?" የሚል ትንሽ በራሪ ጽሁፍ ጻፍኩ። ትምህርት እና ጥበብ ተመሳሳይ እንዳልሆነ ጠቅሻለሁ። በዚህ በራሪ ጽሁፍ ውስጥ አንዳንድ ሰዎችን የሚያስደነግጥ ነገር ጠቅሻለሁ፤በርካታ ዓለም ላይ ያሉ ችግሮች የተፈጠሩት በተማሩ ሰነፎች ነው። በአንድ ወቅት የአሜሪካ ፕሬዝደንት የነበረው ቲዎዶር ሩዝቬልት፤ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር "አንድ ሰው ሌባ ከሆነ፤ባቡርን ይሰርቅ ይሆናል [ሰረገላ ወይም በሃዲድ ላይ የሚሄድ ተሽከርካሪ ልንለው እንችላለን]፤ዳሩ ግን ተመሳሳዩን ሰው ብታስተምሩት፤ሁሉንም የባቡር መንገድ ይሰርቀዋል።" ስለዚህ፤እባካችሁ ትምህርት በጣም ጠቃሚ ነገር ቢሆንም፤ዳሩ ግን ብርሃን እንዳልሆነ አስተውሉ። በእርግጥ፤እንዳልኩት አንዳንድ በጣም የተማሩ አዕምሮዎች ድቅድቅ በሆነ ጭለማ ውስጥ ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል ፍቺ ብቻ ብርሃንን ይሰጣል።

እናም የእግዚአብሔር ቃል ውጫዊ የሆነ ፈውስን ይሰጣል። ይህንን የምናገረው በግሌ ካካበትኩት ተሞክሮ ነው። ወደ መዝሙረ ዳዊት 107 ለአፍታ እንመለስ። ከቁጥር 17 እስከ 20 ድረስ እናነባለን፤

ሰነፎች . . . ስለ ዓመፃቸው ሰነፉ÷ ስለ ኃጢአታቸውም ተቸገሩ።

የተሳሳተ ህይወት በመምራታችን የተነሳ ጉዳት የደረሰባችሁ ሰዎች አላችሁን? በርካታ ሰዎች ለፈውስ ወደ እንደ እኔ እንደመጡ ሰምቻለሁ። በጣም ጥቂት የሆኑት የችግራቸው ምንጭ የተሳሳተ አኗኗራቸው ያመጣው እንደሆነ ሃሳብ ይሰጣሉ። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዓመፃቸው ሰነፉ÷ ስለ ኃጢአታቸውም ተቸገሩ ይላል።

ሰውነታቸው መብልን ሁሉ ተጸየፈች÷ ወደ ሞትም ደጆች ቀረቡ።
በተጨነቁ ጊዜም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ÷ ከመከራቸውም አዳናቸው።
ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም÷ ከጥፋታቸውም አዳናቸው።

እግዚአብሔር ቃሉን ሲልክ ሦስት ነገሮች እንደሚያደርግ አስተውሉ፡እሱ ያድናል፤ከበሽታ ይፈውሳል እንዲሁም ነጻ ያወጣል። የእግዚአብሔር ምህረት ታላቅ ስራዎች—ከሐጢያት ማዳን፤ከበሽታ መፈወስ፤እንዲሁም ከሰይጣን ሃይል ነጻ ማውጣት ነው—በመጀመሪያ በቃሉ የሚፈጽመው ነው።

አንዳንዶቻችሁ፤ይህን ከልምድ አውቀዋለው፤እጆችን በመጫም የሚጸልዩላችሁን ሰባኪያንን ትፈልጋላችሁ፤እናም

ትፈወሳላችሁ።

ደህና ያ ሊሆን ይችላል፤ነገር ግን በርካታ ሰዎች ወደ እኔ መጥተው፤እኔ ብጸልይላቸው እንደሚፈወሱ ያስባሉ። ይሁን እንጂ አይፈወሱም።

በእርግጥ፤እኔ ይህንን ከማስብበት ስፍራ ላይ መጥቻለሁ፤ምክንያቱም በእውነት እነሱ እየፈለጉ ያሉት ወንድም ዴሪክ ፕሪንስን እንጂ ጌታን

አይደለምና።ያለ ሰባኪ እግዚአብሔርን ቃል ከተቀበላችሁ እንደምትፈወሱ ልነግራችሁ እወዳለሁ፤ቃሉን ልኮ ፈወሳቸው ከጠፋታቸውም

አዳናቸው ይላልና።

እንግዲህ ምንም አይነት የህክምና እርዳታ ሊረዳኝ ባልቻለበት ጊዜ ከሆፒታል እወጣ ዘንድ ወደ አገዘኝ የምወደው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ልምጣ፤ምሳሌ 4፤ቁጥር 20፣21 እና 22። ከመደበኛው የኪንግ ጀምስ እትም እጠቅሳለሁ፤ምክንያቱም በዚያ ጊዜ አነብ የነበረው ይህን እትም ነበር፤

ልጄ ሆይ÷ ንግግሬን አድምጥ ወደ ቃሌም ጆሮህን አዘንብል።
ከዓይንህ አታርቃት÷ በልብህም ውስጥ ጠብቃት።
ለሚያገኙአት ሕይወት÷ ለሥጋቸውም ሁሉ ፈውስ ነውና።

የእግዚአብሔር ቃል፤ለስጋችን ሁሉ ፈውስ ነውና ይላል።

ለሰባት ወራት በሆፒታል ውስጥ ነበርኩ። ዶክተሮች ሊያድኑኝ አልቻሉም፤“እምነት ቢኖረኝ እንደምፈወስ እውቃለው።” እል ነበር። እንግዲህ “እምነት ከመስማት ነው፤መስማትም ከእግዚአብሔር ቃል ነው።” የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አገኘሁ። እናም ተስፋ ማድረግ ጀመርኩ፤በአዲስ ተስፋ ቃሉን በሚገባ ማጥናት ጀመርኩ። ነገር ግን አያችሁ፤ችግር ነበረብኝ። እኔ ፈላስፋ ነበርኩ፤የፍስልፍና ባለሙያ ነበርኩ፤የፍልስፍና ስራ የተወሳሰቡ ነገሮችን ቀለል ማድረግ ነው። ለዚያም ነው የሚመረጡት። ስለዚህ፤የእግዚአብሔርን ቃል በቀላሉ መውሰድ አልቻልኩም ነበር። ስለ እግዚአብሔር ፈውስ የተስፋ ቃልን በተስፋ ቃል አነብ ነበር፤ነገር ግን ነፍሴን ስለመፈወስ ብቻ የሚናገር ነው ብዬ አሰብኩ። የታመመውን ስጋዬን በእውነት መፈወስ አይፈልግም፤በቃ መሞቴ ነው አልኩ።

እግዚአብሔር ይመስገን፤ነፍሴ ሆይ፤ሐጢያቴን ሁሉ ይቅር በል፤በሽታዬን ሁሉ ፈውስ፤የሚለው ለነፍሴ ደዌ ብቻ ነው ብዬ አሰብ ነበር። ነገር ግን ምሳሌ 4፤20-22 ያለውን ክፍል ባገኘሁ ጊዜ፤በዚያ ሃሳብ ውስጥ መቆየት አልቻልኩም።

እግዚአብሔር ቃሉን ለሚያገኙአት ሕይወት÷ ለሥጋቸውም ሁሉ ፈውስ ነውና ይላል። እናም ወደ ታች ዝቅ በማለት

ወደ ህዳጉ ተመለከትኩ፤የአማራጭ ንባብ ማድረጌ ለጤናዬ መድሃኒት ነበር። በውትድርና በህክምና ጤና የተዘጋጀ የሚለውን ሆንኩ። ሰዎች ህክምናቸውን እንዴት መውሰድ ይገባቸዋል? ብዬ ጥያቄ አነሳሁ። መልሱ በየዕለቱ ከምግብ በኋላ ለሦስት ጊዜ የሚወሰድ ነው።

ያ የየዕለት ተግባሬ ነበር። ወደ ዝርዝር ጉዳዩ መግባት አልችልም፤ነገር ግን ለሦስት ወይም አራት ወራት የእግዚአብሔርን ቃል እንደ መድሃኒት በቀን ሦስት ጊዜ በየዕለቱ ከምግብ በኋላ እወስድ ነበር፤እናም የተሟላ እና ዘላቂ የሆነ ፈወስ ሰጠኝ እንዲሁም በዓለም ላይ ጤናማ ያልሆነ የአየር ንብረት ባለው ሱዳን ጤና ገባ።

ስለዚህ፤ወንድሞች እና እህቶች እነግራችኋለሁ፤ቃሉ ይሰራል።

አሁን፤ወደ ሦስት እና ከዛ በላይ ወደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ውጤቶች በፍጥነት ልምጣ። ቀጣዩ በሐጢያት እና በሰይጣን ላይ ድልን ማግኘት ነው። መዝሙር 119 ቁጥር 9 እና 11፤

ጉልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል? ቃልህን በመጠበቅ ነው።

እንደገና ቁጥር 11 እንመልከት፤

አንተን እንዳልበድል÷ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ[አከማቸሁ]።

በርካታ፤እጅግ በርካታ የሆኑ ወጣቶች ንጹህ የሆነ ህይወትን መምራት ይቻላል ብለው ይጠይቃሉ።አብዛኛው አስተማሪዎቻቸው እንደማይቻል ይነግሯቸዋል። ጥንቃቄ የተሞላውን የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲያደርጉ ይመክሯቸዋል፤ያ መቼም ጥንቃቄ የተሞላ ሊሆን አይችልም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ለሚኖረው ህይወት ትኩረት ለሚሰጥ ወጣት የእግዚአሔርን ቃል በመጠበቅ ንጹህ የሆነ ህይወት መምራት እንደሚችል ይናገራል።

በአፍሪካውያን ወጣቶች መካከል ስለሰራሁበት ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ እነዚያ ቃላቶች ደጋግመው ሲፈጸሙ አይቻለሁ። የእግዚአብሔርን ቃል በልባቸው በመሰወራቸው ንጹህ እና የተቀደሰ ህይወትን ይመሩ ነበር።

በማቴዎስ ምዕራፍ 4 ኢየሱስን ሰይጣንን ባገኘው ጊዜ የተመለከትነውን ታስታውሳላችሁ፤እሱ በአንድ "ተብሎ ተጽፏል" በሚል መሳሪያ ብቻ ነበር የመታው።

እንደገና፤በፍጥነት ኤፌ 5፤25-27 ያለውን ክፍል እንመለከታለን፤

ባሎች ሆይ÷ሚስቶቻችሁን ውደዱ. . .

ባሎች ሆይ ይህ ምክረ ሃሳብ ሳይሆን ትዕዛዝ እንደሆነ ልነግራችሁ እወዳለሁ፤

ባሎች ሆይ÷ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ፤ በውኃ መታጠብና ከቃሉ ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤
እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።

ኢየሱስ ቅዱስ እና ያለነውር የሆነውን እራሱን እንዴት በኩራት ያቀርባል? በእግዚአብሔር ቃል በኩል በውሃ በመታጠብ ነው።የእግዚአብሔር ቃል ይቀድሰናል፤ያነጻናል።

ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ በውኃ እና በደም የመጣው እሱ ነው ብሎ ይናገር ነበር። በውሃ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በደምም ጭምር እንጂ። በደሙ በከፈለው መስዋዕትነት ዋጀን እንዲሁም ደግሞ በቃሉ ውሃ አነጻን፤ቀደሰን። ሁለቱም ያስፈልገናል። በቃሉ የነጻን እንሆን ዘንድ በደሙ ተዋጅተናል።

በመጨረሻ፤ያዕቆብ እንዲህ ይላል፤ወደዛ አንመለስም፤ነገር ግን በመልዕክቱ፤ምዕራፍ 1፤23-25 መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ መስታወት እንደሆነ ይናገራል። ቃሉን ስታጠኑ፤የሚያሳያችሁ አካላዊ ቁመናችሁን አይደለም፤ነገር ግን በውስጣችሁ ምን እንደምትመስሉ ያሳያችኋል። ያዕቆም እራሳችሁን በመስታወት ስትመለከቱ፤አንድ ስህተት በራሳችሁ ላይ እንዳለ ይጠቁማል፤ ልታስተካክሉ የሚገባችሁን ነገር ማስተካከል አለባችሁ። ጸጉራችሁ ካልተስተካከለ ታበጥሩታላችሁ። ፊታችሁ ያልጸዳ ከሆነ፤ትታጠቡታላችሁ። በመስታወቱ በምታዩት መሰረት ትተገብራላችሁ።ያዕቆብ እንዲህ ይላል፤በእግዚአብሔር ቃል መስታወት ስትመለከቱ ማድረግ ያለባችሁን ታደርጋላችሁ። ውስጣዊ መንፈሳዊ ሰውነታችሁን ተመልክታችሁ እና የሚያሳያችሁን ሁሉ ልታስተካክሉ ያስፈልጋችኋል።

እስቲ ጠቅለል ላድርገውና ልዝጋው። ስምንት የእግዚአብሔር ቃል ውጤቶች።

እምነትን ይሰጣል።

የአዲስ ውልደት ዘር ነው።

መንፈሳዊ ምግብ ነው።

የአዕምሮ ብርሃን ይሰጣል።

አካላዊ ፈውስ ይሰጣል።

በሐጢያት እና ሰይጣን ላይ ድልን ይሰጣል።

መንጻት እና ቅድስናን ይሰጣል።

እንዲሁም፤መንፈሳዊ መስታወት ነው።አሜን።